Ethiopiawinet Radio

Ethiopiawinet.net

ኤፈርት ከቻይና ኩባንያ ጋር የወርቅ ክምችት አገኘ
(በአሰግድ ተፈራ)

በማዕድን ፍለጋ ሥራ የተሰማራ የኤፈርት ድርጅት ኮዮንያ ቤጂንግ ከተባለ የቻይና ኩባንያ ጋር በመሰረተው መከዳ ማይኒንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አማካይነት በትግራይ ክልል የወርቅ ክምችት ማግኘቱ ተገለፀ፡፡ በማዕድን ፍለጋ ሥራ የተሰማሩ ኩባንያዎች በካሳ ክፍያና በአርሶ አደሮች ይዞታ ጉዳይ መቸገራቸውን አስታወቁ፡፡ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር የማዕድን ፈቃድና አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት ባለቤት አቶ ገ/እግዚአብሔር መኮንን እንደተናገሩት መከዳ ኃለፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የወርቅ ክምችትና ብረትነክ ማዕድኖች ያገኘው በምዕራብ መረብ ወንዝ ዳርቻ ጠረር በምትባል ቦታ ነው፡፡

ባለፈው ሐመስ የሚኒስቴር ማሥሪያ ቤቱ የከበሩና ብረትነክ ማዕድናት ላይ የምርመራ ሥራ ከሚሰሩት ባለፈቃዶች ጋር ውይይት ባካሄደበት ወቅት የምርመራ ሥራቸውንና ግኝታቸውን አስመልክቶ ገለፃ እንዲያደርጉ ከተመረጡት ሦስት ድርጅቶች መካከል መከዳ አንዱ ነበር፡፡ እንደ ኃላፊው ገለፃ መከዳ በምርመራ አገኘሁት ያለው የወርቅ ክምችት ቦታ በማዕድን ፍለጋ ቋንቋ "ሊለማ እንደሚችል ተስፋ ሰጪ" ነው ብለዋል፡፡ በማዕድን ፍለጋ ሥራ የተሰማራው መከዳ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የተመሰረተው ኢዛና የተሰኘው የኤፈርት የንግድ ቅርንጫፍ ኮዮንያ ቤጂንግ ከተሰኘ የማዕድን ፍለጋ ሥራ ላይ ከተሰማራ ድርጅት ጋር በጥምር ነው፡፡

በተመሳሳይ ሚድሮክ ጐልድ ኃለፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመተከል አካባቢ ላለፉት ሦስት ዓመታት ባካሄደው የማዕድን ፍለጋ የወርቅ ክምችት ማግኘቱን፣ ክምችቱ የተገኘበት ቦታ ሊለማ እንደሚችል የድርጅቱ ባለሙያ ገለፃ አድርገዋል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ገለፃ ያደረገው ጐልደን ፕሮስፔክት ማይኒንግ የተሰኘው የእንግሊዝ አገር ኩባንያ በምሥራቅ ወለጋ ነጆ አካባቢ ቱሉ ካፒ በሚባል ቦታ 22.3 ቶን የወርቅ ክምችት ማግኘቱን፣ በቀሩት ቦታዎች ላይ የሚካሄደው ተጨማሪ የማዕድን ፍለጋ ሲጠናቀቅ የክምችቱ መጠን ወደ 30 ቶን ያድጋል ተብሎ እንደሚጠበቅ በባለሙያዎቹ ገለፃ አድርጓል፡፡ ከገለፃዎቹ በኋላ በተካሄደ ውይይት የተሳተፉት 54 የተለያዩ የማዕድን ፍለጋ ፈቃድ ያወጡ፣ የ28 ኩባንያዎች ባለቤቶች በውይይቱ ወቅት በማዕድን ፍለጋ ሥራው ላይ ያጋጠማቸውን ችግር እንዳቀረቡ አቶ ገ/እግዚአብሔር ተናግረዋል፡፡

የማዕድን ጉድጓድ ቁፋሮዎች በ20 ሜትር ርቀት በብዛት ስለሚቆፈሩ የመኖሪያ ቤቶችንና የአርሶ አደሮችን ይዞታ ስለሚነካ አርሶ አደሮቹ ለኩባንያዎቹ የካሳና የግምት ጥያቄ በማቅረብ ጫና እንደሚፈጥሩባቸው፣ ይህንን ችግር ሊፈታው የሚችለው መንግሥት በመሆኑ አንድ መፍትሔ እንዲሰጣቸው በማዕድን ሥራ ላይ የተሰማሩት ጠይቀዋል፡፡ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር አቶ አለማየሁ ተገኑ ችግሩን ለመፍታት ቀላል ባይሆንም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ክልሎችና የአስተዳደር አካላት ጋር በመነጋገር ችግሩ እንደሚፈታ በመግለፅ መልስ መስጠታቸው ታውቋል፡፡

በሌላ ዜና በማዕድን ሥራ ለመሰማራት ፈቃድ አውጥቶ በቤንሻንጉል ክልል ሦስት ብሎኮች ላይ ሥራ ጀምሮ የነበረው ሜናገም የተሰኘ ኩባንያ በዓለም ላይ የተፈጠረውን የገንዘብ ቀውስ ምክንያት በማድረግ ፈቃዱእንዲሰረዝለት ጥያቄ ማቅረቡን አቶ ገ/እግዚአብሔር ተናግረዋል፡፡ ኃላፊውእንዳሉት የኩባንያውጥያቄ በህጉ መሠረት ማጣራት ይደረግበታል፡፡